# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 218 ሐምሌ 12 2004 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ እንዲኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዛሬውኑ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ትግል እንዲቀላቀል በይፋ ጥሪ ያደርጋል።

ትግሉ የሁላችን፤ ድሉም የጋራችን ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## መለስ ዜናዊ በቤልጂዬም ሆስፒታል ውስጥ ከሞት ጋር እየተፋጠጠ ባለበት በአሁኑ ሰዓት በረከት ስምዖን በዕረፍት ላይ ነው ሲል ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጠ

ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በገጠመላቸው ሳንባ ከሚተነፍሱት የወያኔ ባለሥልጣናት አንዱ የሆነው በረከት ስምዖን ከትናንት በስቲያ ሃሙስ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ከሞት ጋር ግብግብ በመግጠም ላይ የመሆኑ ዜና በመላው አለም የተሰራጨውን አለቃውን ከሥራ ብዛት ጋር በተያያዘ ድካም እረፍት ላይ ነው በማለት የተለመደ ውሸቱን እንደገና ለኢትዮጵያ ህዝብ አሰምቶአል።

በመለስ ዜናዊ በድንገት ከመካከላቸው መለየት የተደናገጡትና የሚይዙ የሚጨብጡትን ያጡ የህወሃት መሪዎች ይህንን ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት ለረቡዕ ጠርተውት የነበረውን በሰረዙ ማግስት በወያኔ ሚዲያ ውስጥ የሚሰሩትን ጋዜጠኞች በአስቸኳይ ጠርቶ መግለጫውን የሰጠው በረከት ከድንጋጤው ብዛት ጎሮሮው እየደረቀ በያንዳንዱ አረፍተነገር መካከል ውሃ ሲጋትና ሲያስል ተስተውሎአል። ከዚህም በተጨማሪ መለስ በህመም ላይ ሳይሆን በ እረፍት ላይ ነው፤ እረፍቱንም እንደጨረሰ ወደ ሥራው ይመለሳል በማለት መግለጫውን ከጀመረ ቦኋላ የራሱ ጋዜጠኞች ወጥረው ሲይዙት ቀደም ብሎ በመጋቢያው የሰጠውን በመጻረር በህመም ምክንያት ህክምና ላይ መሆኑንና ህክምናውን በቅርቡ ጨርሶ እንደሚመለስ ተናግሮአል። መለስ የሚታከምበት ቦታ አገሩንና የሆስፒታሉን ስም ህዝብ ከተለያዩ ሚዲያዎች እየሰማ መሆኑን ሰምቶ የሚያውቅ የማይመስለው በረከት ይባስ ብሎ አለቃው ያለበትን አገር እንዲናገር ሲጠየቅ "ለደህንነቱ ሲባል ለመናገር አልፈልግም" በማለት የተለመደውን ትዝብቱን ተከናንቦአል።

የበረከት ስሞኦንን ጋዜጣዊ መግለጫ ለመዘገብ በቦታው የነበሩ ጋዜጠኞችም ይሰጥ በነበረው ቅጥፈትና ውሸት የመደነቅና የመሳቀ ምልክቶችን ያሳዩ እንደነበሩ በኢትዮጵያ ቴለቪዥን ከተላለፈው ምስል ለማየት ተችሎአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የመብት ጥያቄ ከፍ ወደ አለ አዲስ ደረጃ መሸጋገሩ ተገለፀ

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የእምነት ነፃነትን፣ መሪዎቻቸውን በነፃነት የመምረጥ መብትን እና ወያኔ በእስላማዊ ተቋሞች ላይ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት ለማስቆም የጀመሩት ተቃውሞ ሰባተኛ ወሩ ይዞዓል። በእነዚህ ጊዜዓት ውስጥ የሙስሊም ወገኖቻችን ትግል ብዙ ፈተናዎችን አሳልፏል። ሙስሊም ወገኖቻችን ያሳዩት ጽናት ኢትዮጵያዊያን ያኮራ ሲሆን በዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ላይ ደግሞ ከፍተኛ ሽብር ፈጥሯል።

ወያኔ የማፈግፈግ ምልክቶችን ያሳየው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መሪዎቹን እንደና እንዲመርጥ በመፍቀድ ሲሆን ይህም ያደረገው የምርጫውን ውጤት ለመዘረፍ እንዲመቸው ምርጫው በቀበሌዎች እንዲሆን በማስገደድ ነበር። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ግን ይህን ማሳሳቻ ሳይቀበል ትግሉን አጠናክሮ ቀጠለ። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ትግል የክርስቲያኖችንም ድጋፍ እያገኘ መምጣቱ በወያኔ ሰፈር ከፍተኛ መደናገጥን ፈጠረ።

ባለፈው ሣምንት በአወሊያ መስጊድ ሊተደገር የታሰበ የሰደቃና የፀሎት ፕሮግራም የፌደራል ፓሊስ አስለቃሽ ጪስ ጭምር ተጠቅሞ በተነው። በዚህ ቀን ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ኢትዮጵያዊያን ሕይታቸውን እንዳጡ ይነገራል። በርካቶች ቆስለዋል፡ ብዙዎች ደግሞ ተደብብደዋል።

በመቶዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ታስረል። የወያኔ የፌደራል ፓሊስ በምዕመናን ላይ ያደረሰው የጥቃት መጠን ግምት እንኳን ለመስጠት በማይቻል ሁኔታ ዜናዉን አፍኗል። ጋዜጠኞች እቦታው እንዳይደርሱ አድርጓል። ተጎጅዎችን ፓሊሶች ወዴያውኑ እያነሱ የት እንዲያደርሷቸው አይታወቅም። "በጠላት ጦር የተወረርን ይመስላል" ይላሉ በቦታው የነበሩት አንድ አባት። "ብዙ ሰዎች በጥይት ተመተው ሲወድቁ በዓይኔ አይቻለሁ። ይዳኑ፣ ይሙቱ ግን አላውቅ" ይላሉ ሌላኛዋ ታዛቢ።

የሰደቃው ፕሮግራም በአወሊያ እንዳይካሄድ ቢከለከልም (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የሚከፈለውን መስዋ ዕትነት እየከፈልን ትግሉን ወደፊት እንገፋለን ሲል አንድነት መግለጫ አወጣ

ፓርቲው ይህንን የገለጸው ሰላማዊ ትግል በአፈናና በእንግልት ሊቀለበስ አይችልም በሚል ባወጣው መግለጫ ሲሆን በማያያዝም ሀምሌ 6 ቀን 2004 ዓ.ም የወያኔ ፍርድ ቤት በእነ አንዱዓለም አራጌ ፋይል ክስ በተመሰረተባቸው ወንድሞቻችን ላይ ከ13 ዓመት እስከ እድሜ ልክ የሚደርስ የቅጣት ውሳኔ አስተላልፎባቸዋል፤ ይህ ፍርድ ቤቱ የሰጠው የቅጣት መጠን የሚያስተላልፈው መልዕክት ካለ የስርዓቱን ጨካኝነት እና ለስልጣኑ ስጋት ነው የሚለውን ማንኛውንም ዓይነት እንቅስቃሴ ከማፈንና የፍትሕ ሥርዓቱን በማን አለብኝነት በማጥቂያ መሣሪያነት ከመጠቀም ወደ ኋላ የማይል መሆኑን ብቻ ነው ሲል አስረድቷል።

በተከሳሾች ላይ ለፍርድ ቤት የቀረቡት ማስረጃዎች ከፍተኛ ችሎታና ልምድ ባላቸው የህግ ባለሞያዎች ሲመዘኑ እስከ እድሜ ልክ እስራት የሚያስቀጡ ሊሆኑ ቀርቶ ለምክርና ለተግሳፅ እንኳን የማያበቁ ናቸው ነገር ግን ከፍርድ ቤቱ ትንታኔ መረዳት እንደተቻለው በሽብርተኝነት ስም ዜጎችን ከማንኛውም ዓይነት ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ ለመገደብና በዓረብ ሀገራት የታየው ዓይነት ህዝባዊ እንቅስቃሴ በማንኛውም ሁኔታ በኢትዮጵያ እንዳይከሰት ወያኔ እየተከተለው ያለው አቅጣጫ አካል ነው ብሏል።

እንደ መግለጫው አስር ወራት የፈጀው ፖሊስ፣ ዓቃቢ ህግ፣ ፍርድ ቤት እንዲሁም በመንግሰት በሞኖፖል የተያዘው ሚዲያ በመተጋገዝ በጋራ ሲያከናውኑት የነበረው የተቀነባበረ የኢ-ፍትሐዊነት ድራማ የመጀመሪያው ምዕራፍ በፍርደገምድል የጥፋተኝነት ውሳኔና ጭካኔ በተመላበት የቅጣትፍርድ ተጠናቋል:: ይሁንና የድራማው ደራሲ፤ አዘጋጅና መሪ የሆነው ወያኔ ዕቅዱ በአሰበው መንገድ ተሳክቶለታል ማለት አይደለም::

ይልቁንም ለስርዓቱኢ-ዲሞክራሲያዊነት ማረጋገጫ ከመስጠቱም ሌላ ከምንግዜውም በላይ በርካታ ወጣት ታጋዮች ወደ ድርጅቱ እንዲቀላቀሉ አድርጓል።

ዛሬ በኢትዮጵያ ሠላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ የማይቻል ሆኗል:: የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት ሕልም ሆኖ ቀርትዋል:: ሙስና የሥርዓቱ ዓይነተኛ ባህሪ ነው። በመንግሥት ጣልቃ ገብነት ምክንያት የሃይማኖት ተቋማት በሙብታቸውና ዕምነታቸው በሚፈቅድላቸው መሠረት መንቀሳቀስ አልቻሉም:: (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚንስቴር በልጂየም ውስጥ ከሞት ጋር ትንቅንቅ ይዞአል ሲል ዘት ኦን ላየን ዘገበ። የወያኔ ኮሚኒኬሽን ሚንስትር በበኩሉ የጤንነቱን ሁኔታ ለመግለጽ ጠርቶት የነበረውን ጋዜጣዊ መግለጫ ሰረዘ

በካንሰር ህመም ምክንያት አእምሮውን ከሳተ ቦኋላ ወደ ቤልጂዬም የተወሰደው መለስ ዜናዊ ከህመሙ ማገገም እንደማይችል የተለያዩ አለም አቀፍ ሚዲያዎች እየዘገቡ ነው። መለስ ዜናዊ ብራሰል የገባው ከሁለት ሳምንት በፊት በፈረንጆች አቆጣጠር ጁላይ 5 ጠዋት ሲሆን የግንቦት 7 ድምጽና የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ዜናውን በስፋት ካሰራጩ ጥቂት ቀናት ቦኋላ ባለፈው ቅዳሜና እሁድ አድስ አበባ ውስጥ ተካሂዶ በነበረው የአፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ላይ አለመገኘቱ በፈጠረው ትኩረት የአገር ውስጥና የውጪ ሚዲያዎች ዜናውን ተቀባብለው በአለም ላይ እያዛመቱት ነው።

ቀደም ሲል ዜናውን የአክራሪዎችና የጽንፈኞች የፈጠራ ወሬ ነው እስከማለት ደርሰው የነበሩ የወያኔ ባለስልጣናትም በ ቁጥጥራቸው ሥር በሚገኙ መገናኛ ብዙሃንና በአፍቃሪዎቻቸው ድህሬ ገጽ ላይ ህመሙ ለከፋ የማይዳርግ ቀላል ነው በማለት ፈራ ተባ እያሉ ካለፈው ሰኞ ጀምሮ የሰጡት መግለጫ አገር ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት በመሳቡ ህዝቡን ለማረጋጋት ሲባል ኦፊሴላዊ የሆነ ጋዜጣዊ መግለጫ በትናንትናው ዕለት ለመስጠት አቅደው እንደነበረና ምክንያቱ ባልተገለጸ ሁኔታ ፕሮግራሙን መሰረዛ ታውቆአል።

ለዝግጅት ክፍላችን በደረሰው መረጃ መሰረት ጋዜጣዊ መግለጫው ተጠርቶ የነበረው ህወሃቶች ለሃይለማሪያም ደሳለኝ በሰጡት የተሳሳተ መረጃ ህመሙ ቀላልና በቅርቡ ተሽሎት ወደሥራው ይመለሳል የሚለውን በኦፊሴላዊ መንገድ ለህዝብ ለመግለጽ ታስቦ ነበር። ሆኖም ከአገር ውጪ ወደ አገር በሚተላለፉ ሚዲያዎችና እንደ ፊስ ቡክ በመሳሰሉት ማህበራዊ ሚዲያዎች መለስ ዜናዊ ከህመሙ ተሽሎት የመነሳቱ ተስፋ የጨለመ መሆኑ በሰፊው በመዘገቡ በተለመደው የነመለስ በረከት ቅጥፈትና አይናችሁን ሽፍኑ ላሞኛችሁ ቀልድ መቀጠል እንደማይቻል የተረዱ የህወሃት የውስጥ

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ትግሉም ድሉም የጋራ ነው!!!

### ክርስቲያን ኢትዮጵያዊያን የሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን ትግል እንዲቀላቀሉ የቀረበ ጥሪ

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ለሰባት ተከታታይ ወራት ሲያደርጉት የነበረው ሃይማኖታዊ መብቶችን የማስከበር ትግል፣ ወያኔ በወሰደው አረመኔያዊ እርምጃ ምክንያት ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግሯል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ሲገልፀው እንደነበረው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ የሙስሊሞች ብቻ አይደም። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ጥያቄ ነው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ለሙስሊም ወገኖቻችን የእምነት መብቶች ጥያቄ የሰጠው የጥይት ምላሽ የጥያቄዎቻቸውን ደረጃ አሳድጎታል። ቀድሞ የሙስሊሞች ጥያቄ "የእምነት መብቶቻችን ይከበሩ" "መንግሥት በሃይማኖታችን ጣልቃ አይግባ"፤ "መሪዎቻችንን እኛው ራሳችን እንድንመርጥ ይፈቀድልን"፤ "እኛም እንደ ዜጋ የመሰማት መብት አለን" እና የመሳሰሉት ነበሩ። አሁን ግን ጥያቄው በሕይወት የመቆየትና እንደ ሰው የመቆጠር ጉዳይ ነው። ዛሬ የሙስሊም ወገኖቻችን ጥያቄ በኢትዮጵያ ውስጥ በሕይወት የመኖር መብት ጥያቄ ሆኗል።

በተፈጠረው አዲስ ሁኔታ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ የሰው ልጆች ሁሉ ጥያቄ ሆኗል።

በአገራችን በሚገኙ የተለያዩ ሃይማኖቶች ምዕመናን መካከል ከዚህ በፊት ከነበረው እጅግ የላቀ መቀራረብ እየታየ መሆኑ እውነት ነው። ቀድሞ የነበረው መከባበር ዛሬ ወደ መደጋገፍ አድጓል።

ለምሳሌ:-

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመለስ ዜናዊ ገዳይ ቡድን በአወሊያ መስጊድ ውስጥ በነበሩት ሙስሊሞች ላይ ጭካኔ የተሞላበት ጥቃት ባደረሰበት ወቅት ክርስቲያኖች አቅማቸው የቻለውን ያህል የመከላከል እርምጃ ወስደዋል። አብረው ተደብድበዋል፤ ቆስለዋልም።
2. በአንዋር መስጊድ ተመሳሳይ ዝግጅት በነበረበት ወቅት የሙስሊም ወገኖቹ ድምጽ ጎልቶ እንዲሰማ አጠገቡ ያለው የራጉኤል ቤተክርስቲያ የድምጽ ማጉያውን አጥፍቷል።
3. በደሴ ከተማ ሙስሊሞች ላደረጉት ሰደቃ ክርስቲያኖች ድንኳን በነፃ ሰጥተዋል፤ እንጀራና ለስላሳ መጠጦችን በማዋጣት ተባብረዋል።

በውጭ አገርም ተመሳሳይ መደጋገፍ እየታየ ነው።

ለምሳሌ፡-

1. በስደት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ የመብት ጥያቄ መሆኑን በመረዳት ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ከጎናቸው እንዲቆሙ ጥሪ አድርጓል።
2. ወያኔ በዋልድባ ገዳም ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት በመቃወም በሰሜን አሜሪካ እና አውሮፓ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ከክርስቲያን ወገኖቻቸው ጎን ቆመው "ዋልድባ ታሪካዊ ቅርሳችን ነው፤ መደፈር የለበትም" እያሉ ድምፃቸውን አሰምተዋል።
3. በደቡብ አፍሪቃ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ደጋፊዎች በጠሩት ስብሰባ ውስጥ አንድ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መምህር ሙስሊም ኢትዮጵያን ለሚያደርጉት ተጋድሎ አጋርነት ለመግለጽ "ሁላችን በአንድ ቃል ፈጣሪን እናመስግን" በማለት "አላሁ አክበር!" ሲሉ የአዳራሹ ተሰብሳቢ በሙሉ አብሯቸው "አላሁ አክበር" ብሏል።

ይህ በጣም አበረታች ነው። ሆኖም አሁን ለደረስንበት የትግል ደረጃ በቂ አይደለም።

ሙስሊም ወገኖቻችን በጽናት እየታገሉ ነው። በዚህም ምክንያት የጥይት አረር እየዘነበባቸው ነው። ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ ሙስሊም ወገኖቻችን ሕይወታቸውን አጥተዋል፤ በርካቶች ቆስለዋል። ሕፃናትና ሴቶች ሳይቀሩ ተድብድበዋል፤ በጅምላ ታፍሰው ታስረዋል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የክርስቲያን ኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ አሁን ከአለበት ደረጃ በላይ መሆን ይገባዋል። የኢትዮጵያ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ እያቀረበ ያለው ጥያቄ የሙስሊሙ ብቻ አይደለም። የሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ጥያቄ በገዛ አገሩ ተከብሮ እንዲኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ጥያቄ ነው። የሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ጥያቄ የሰው ልጆች ሁሉ ጥያቄ ነው።

ክርስቲያን ኢትዮጵያዊያን ድጋፍ መስጠት ሳይሆን ትግሉን ሊቀላቀሉ ይገባል። የሙስሊም ኢትዮጵያን ትግል የሁላችንም ትግል ነው። የትግሉ ውጤትም የጋራችን ነው። በሰው ልጅነት፣ በኢትዮጵያዊነት አንድ ነን። ሁላችንም ፍትህን፣ ነፃነትን፣ እኩልነት፣ ዲሞክራሲን እንሻለን።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነትና ዲሞክራሲ እንዲኖር የሚፈልግ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዛሬውኑ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ትግል እንዲቀላቀል በይፋ ጥሪ ያደርጋል።

ትግሉ የሁላችን፤ ድሉም የጋራችን ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## መለስ ዜናዊ በቤልጂዬም ሆስፒታል ውስጥ ከሞት ጋር እየተፋጠጠ ባለበት በአሁኑ ሰዓት በረከት ስምዖን

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሪፖርተር ባለፈው ረቡዕ ባወጣው ዘገባ መለስ ዜናዊ ህክምና እያደረገበት ባለበት አገር ሂደው ጎብኝተውት ተመልሰዋል ካላቸው የወያኔ ባለሥልጣናት አንዱ በረከት ስምን የነበር ቢሆንም የግንቦት 7 ድምጽ ባደረገው ማጣራት አንድም የወያኔ ባለስልጣናት ይህ ሪፖርት እስከ ተጠናከረበት ሰዓት ድረስ ሰውየውን እንዳልጎበኘ ለማረጋገጥ ችሎአል።

መለስ ዜናዊ ከ3 ወር በላይ በህይወት መቆየት እንደማይችል ቀደም ሲል ከወር በፊት በሃኪሞቹ ተነግሮት ወደ አገር ቤት እንደተመለሰ የሚናገሩ ምንጮች ኮማ ውስጥ ገብቶ ተመልሶ ወደ ቤሊጂዬም ሆስፒታል ከመጣ ወዲህ እራሱን መቆጣጠር ስለማይችል አንድም ጎብኚ ወደተኛበት ክፍል ገብቶ አያውቅም።

## የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የመብት ጥያቄ ከፍ ወደ አለ አዲስ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ፕሮግራሙ በአንዋር መስኪድ በተሳካ ሁኔታ ተካሂዷል። ይህ ደግሞ ወያኔ ሊሸከመው የማይችል ውርደትን ስላከናነበው ወደ ፋሽስታዊ እርምጃው እንዲያመራ ገፋፋው። በዚህም ምክንያት ከ70 በላይ የሙስሊን መሪዎች መታሰራቸው በሸብር ነጋሪው ቴሌቪሽን ተነገረ።

ከሙስሊሙ አመራር እንደተሰማው ከሆነ ወያኔ 70 ሰዎችን አስሬዓለሁ ቢልም በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ የታሰሩት ሙስሊሞች ቁጥር ከ200 በላይ ይሆናል።

ግንቦት 7 እና ሌሎችም የኢትዮጵያ ፓለቲካ ድርጅቶች ከሙስሊሞች ጎን መቆማቸውን በተደጋጋሚ መግለጫዎቻቸው አረጋግጠዋል። በስደት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስም የሙስሊም ወገኖቻችን የመብት ጥያቄ በመደፍ ተደጋጋሚ መግለጫዎችን አውጥቷል።

በአርቡ የረመዳን የመጀመሪያ ቀን በአንዋር መስጊድ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ምዕመናን ተገኝተው በአስደናቂ ድርጅታዊ ብቃት ተቃሙሞዓቸውን እጅ ለእጅ በመያያዝና በዝምታ ገልፀዋል።

ሁኔታው ያስፈራው ዘረኛው አገዛዝ በግፍ ካሰራቸው የሙስሊም መሪዎች ጥቂቶቹን መፍታት እየተሰማ ነው።

በተያያዘ ዜና አርብ እለት መውጣት የነበረባቸው "ሰለፍያ" እና "ሰውቱል እስላሚያ" የተባሉት የሙስሊም ጋዜጦች፣ እንዲሁም "አልቁዱስ" የተባለው የመጅሊስ ደጋፊ ጋዜጣ ሳይታተሙ ቀርተዋል። የሰለፊያ ጋዜጣ ቢሮ ሌሊት በፖሊስ ተከቦ ሲበረበር እንደነበር የደረሰን ዜና ያረጋግጣል።

የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ተጋድሎ በሚመለከት አስተያየት የሰጠናቸው ባለሙያዎች "ከእንግዲህ የሙስሊሞች ትግል የሙስሊሞች ብቻ አይደለም። ትግሉ የኢትዮጵያዊያን ሁሉ ነው። ስለሆነም በአሁን ጀምሮ ሃይማኖት ሳይለይ ነፃነትና እኩልነት ናፋቂ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአንድነት መቆም ይኖርበታል" በሚል ሃሳብ ይስማማሉ።

ንቅናቄዓችን በዚህ ሣምንት ርዕሰ አንቀሱ "ትግሉም ድሉም የጋራ ነው!!!" በሚል ርዕስ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊያን የሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን ትግል እንዲቀላቀሉ ጥሪ ማቅረቡ ይታወሳል።

## የእምነት ነፃነት፤ የሰብዓዊ መብቶች አካል ነው

የግንቦት 7 ድምጽ በርዕሰ አንቀጽ ቁጥር 185 አውጥቶት የነበረ

በዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 18 መሠረት እያንዳንዱ ሰው በግሉም ሆነ በጋራ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተልና የማስተማር፤ ያልፈለገውን ደግሞ የመተው መብት አለው።

እንደሚታወቀው፤ ሰብዓዊ መብቶች እርስ በርሳቸው የተቆራኙ፤ እርስ በርሳቸውም የሚደጋገፉ ናቸው። አንዱ የመብት ዓይነት ሲጓደል፤ ሌላውም አብሮ ይጓደላል። ለምሳሌ የመናገር መብት ተገፎ እያለ የማምለክ መብት ሊፋፋ አይችልም፤ ወይም ደግሞ ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብት ተጥሶ እያለ የማምለክ መብትን የሚያስከብር ተቋም ሊኖር አይችልም። ለዚህም ነው ሰብዓዊ መብቶች የማይነጣጠሉ ናቸው የሚባለው።

በአገራችን እየተባባሰ የመጣው በእምነት ላይ ያለው ግልጽ አፈና በአጠቃላይ በሰብዓዊ መብቶች ላይ ያለው አፈና አንድ ዓይነተኛ መገለጫ ነው። አገዛዝ በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር የነበረባቸው ተቋማት ሰብዓዊ መብቶችን መርገጫ እንደሚሆኑ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሥር ያለችውን አገራችንን ማየት በቂ ነው። በአገዛዙ ሥር ያሉ ፍርድ ቤቶች እየሠሩ ያሉት ምንድነው? ምንድነው "የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን" እየሠራ ያለው? ምንድነው "የሕዝብ እንባ ጠባቂ ኮሚሽን" እየሠራ ያለው? ምንድነው ፓሊስ፣ ምርጫ ቦርድና ፓርላማ እየሠሩ ያሉት? ጥያቄዎቻችንን መቀጠል እንችላለን። ምላሹ ግን አንድ ነው። እነዚህ መሰል ተቋማት በአገዛዝ ሥር ሲወድቁ የሰብዓዊ መብቶች መርገጫ እንጂ ማስከበሪያ ሊሆኑ አይችሉም። በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ውስጥ ደግሞ  እነዚህ ተቋማት የአፈና ብቻ ሳይሆን የዘረኝነትም ማስፋፊያ ናቸው።

የአገዛዝ ሥርዓት አፈናውን ባጠናከረ መጠን የመንግሥት ተቋማትን ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ተቋማትንም ጭምር የጭቆናው መሣሪያ ያደርጋቸዋል።  ለዚህ ደግሞ ገሃድ ምሳሌ የሃይማኖት ተቋማቶቻችን ናቸው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ በሁሉም ሃይማኖቶች ተቋማት ውስጥ የራሱን ካድሬዎች በመሾም ምዕመናኑን ለመቆጣጠር ጥረት ማድረግ የጀመረው ሥልጣን ኮርቻ ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የእምነት ተቋማት መሪዎች ከእምነት መሠረታዊ መርሆዎች ያፈነገጡ ተግባራትን ሲተገብሩ ማየት እጅግ የተለመደ ነገር እየሆነ መጥቷል።

በእምነቶችና በእምነት ተቋማት ላይ እየደረሰ ያለው በደል ሁሉንም ሃይማኖቶች ያዳረሰ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በእስልምና ሃይማኖትና በሙስሊም ማኅበረ -ሰብ ላይ እየደረሰ ያለው አፈና ግን ከሁሉም የከረረ እና የመረረ ሆኗል። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የመጅሊስን አመራር በራሱ ካድሬዎች  ከማስያዝ በላይ በዝርዝር ሃይማኖታዊ አስተምህሮት ውስጥ በመግባት አንዱን ጀማ ወዳጅ፤ ሌላኛውን ደግሞ ጠላት እያደረገ ነው።

ዘረኛው አገዛዝ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታዮችን ከማጋጨት አልፎ በአንድ ሃይማኖትም ውስጥ የተለያዩ ጎራዎች እንዲፈጠሩና እርስ በርሳቸው እንዲጋጩ እያደረገ ነው። ይህ አካሄድ እጅግ ከፋት የተሞላበት ውጤቱም አደገኛ የሆነ ነገር ነው።

ለምንድነው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በአሁኑ ሰዓት በተለይ በእስልምና ሃይማኖትና በሙስሊም ማኅበረሰብ ላይ ያነጣጠረው? ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የሚከተሉት ሁለቱን ብቻ ማንሳት ይበቃል።

- መለስ ዜናዊ "ሙስሊም ለፓለቲካ ደንታ የለውም" የሚል የትዕቢት አስተሳሰብ ተቆራኝቶት ቆይቷል። ሆኖም ግን እያለቀ ባለው የአውሮፓውያን ዓመት በሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ እየታዩ ያሉ ለውጦች መለስንና የመለስ ዓይነት ሰዎችን መግቢያ ቀዳዳ አሳጥቷቸዋል። የሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ አብዮቶች ሙስሊም ወገኖቻችን ለፍትህና ለዲሞክራሲ ያላቸውን ጥማት ብቻ ሳይሆን ቁርጠኝነታቸውንም አጉልቶ አሳይቷል። መለስ ዜናዊና ጋሻ ጃግሬዎቹ አሻግረው እያዩት ያለው ሕዝባዊ ማዕበል እንዳይውጣቸው መፍትሄ አድርገው ያቀረቡት ሙስሊሙን መከፋፈል ነው።
- የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል የከረረ ጥል ለመፍጠር ያልቆፈረው ጉድጓድ የለም። በተለይም ሙስሊሙንና ክርስቲያኑን ማኅበረሰብ ለማቃቃር ብዙ ጥሯል። በሰኔ 2001 በደሴ አርሴማ ቤተክርስቲያን ግንባታ ሰበብ ሆነ ብሎ ያስነሳው ጠብ አንዱ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ሆኖም ግን መለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑ በፈለጉት መጠን ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች አልተጣሉም። ጊዜዓዊ ግጭቶችም በተከበረው አገራዊ የሽምግልና ባህል እየተፈቱ እርቅ የሚወርድ በመሆኑ መለስ አዲስ እና የከፋ ዘዴ መሸረብ ነበረበት። አዲሱ ዘዴ፣ የእያንዳንዱ ሃይማኖት አማኝ እራሱ ከራሱ ጋር እንዲጣላ ማድረግ ሆነ።

ግንቦት 7: የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አሁን የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በእስልምና ሃይማኖት ላይ እየተሞከረ ያለው አደገኛ ጣልቃ ገብነትን አጥብቆ ይቃወማል። አደጋው በእስልምና ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ሃይማኖቶችም ላይ ነው፤ በእስልምና ላይ እየተሞከረ ያለው ከተሳካ ነገ ወደሌሎቹም ይዛመታል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የአምልኮት ነፃነት ማጣት የሰብዓዊ መብት እጦት መሆኑን ሁላችንም መረዳት ይኖርብናል። መፍትሄም የሚገኘው በተናጠል ሳይሆን በጋራ ነው። ልናስከብረው የሚገባ መብትም ሰብዓዊ መብቶችን በሙሉ ነው።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ተወግዶ ዲሞክራሲያዊ እና ፍትሃዊ ሥርዓት ሳይገነባ ሰብዓዊ መብቶች መከበር የማይችሉ በመሆኑ ትኩረታችን በዋነኛው የጋራ ጠላታችን በሆነው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ላይ መሆን ይኖርበታል።

ሙስሊሙ ወገናችን፣ ሰብዓዊ መብቶች ሳይከበሩ የሃይማኖት ነፃነት ብቻውን መከበር የማይችል መሆኑን ተረድቶ መለስ ዜናዊን ለማስወገድ በምናደርገው የጋራ ትግል በጽናት እንዲቆም ግንቦት 7 ጥሪ ያደርጋል።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ሳይወገድ ሰብዓዊ መብቶችን ማስከበር ስለማንችል አንድነታችንን አጠንክረን የነፃነት ትግላችንን እናፋፍም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

## የሚከፈለውን መስዋ ዕትነት እየከፈልን ትግሉን ወደፊት እንገፋለን

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በጥቅሉ ይህ ሥርዓት ሕዝቡ የእኔ የማይለውና በላዩ ላይ በጉልበት የተጫነበት ነው የሚለው መግለጫው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደራጀም ሆነ በአልተደራጀ መልኩ የእሱ ያልሆነውንና በኃይል የተጫነበትን የወያኔ ሥርዓት ወደሚገባው የታሪክ ሥፍራ ለመላክ ጠንክሮ እንዲታገል መልእክት አስተላልፏል።

አንድነት አያይዞም በውጭው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ደጋፊዎቹ ግፈኛው ሥርዓት የደገሰላቸውን መራራ የግፍ ፅዋ እየተጎነጩ ያሉት ታጋዮች የሚያሳዩትን ጠንካራ የትግል መንፈስ ስንቅ በማድረገግ ሰላማዊ ትግሉን ከምን ጊዜም በላይ አጠናክሮ እንዲቀጥል ለትግሉ የሚያስፈልገውን ዘርፈ ብዙ ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋሉ ብሎ እንደሚያምን ገልጾ በተለይ የታሳሪ ታጋዮች ቤተሰቦችና ልጆቻቸው በግፈኛ ውሳኔ ምክንያት ችግር ላይ እንዳይወድቁ የሚቻለው ድጋፍ ሁሉ እንዲደረግላቸው ጥሪ አቅርቧል።

የፓርቲው መግለጫ በመጨረሻ የታጋዮች እስር ለሰላማዊ ትግል አራማጆች የትግሉ ፍሬ ማፍራት ምልክት ሲሆን ለጨቋኞች ደግሞ የፍርሃታቸውን ጥግ የሚያሳይ ብቻ መሆኑን በማብራራት ሠላማዊ ትግል በእስርና እንግልት እንደማይቀለበስ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በተለይም ለገዢው ፓርቲ ማረጋገጥ እንደሚወድ ገልጿል።

## የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚንስቴር በልጂየም ውስጥ ከሞት ጋር ትንቅንቅ ይዞአል .

. . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሃይሎች ጋዜጣዊ መግለጫው እንዲዘገይ ትዕዛዝ በማስተላለፋቸው ዕቅዱ ሌላ ቀን ተላልፎአል በሚል ሰበብ ለመሰረዝ በቅቶአል።

በረከት ስምኦን ለአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ የዜና ወኪል በሰጠው አጭር ቃል መጠይቅ አለቃው መለስ ዜናዊ በህመም ላይ መሆኑን አምኖ የጤንነቱ ሁኔታ ግን ለከፋ የማይሰጥና ታክሞ እንደጨረሰ ወደሥራው እንደሚመለስ መናገሩን የገለጸ ሲሆን የዜና ወኪሉ ግን ከዲፕሎማቲክ ምንጮች አገኘሁት ባለው መረጃ የበረከትን ምስክርነት ቃል በማጣጣል ለህይወት አስጊ በሆነ ደረጃ ላይ መድረሱን ዘግቦአል።

የመለስ ዜናዊ ጤንነት መልሶ የማገገም ተስፋ እንደሌለው የዘገበው ሌላው የዜና አውታር ቢቢሲ ደግሞ በበኩሉ የወያኔ ባለሥልጣን የሚሰጡትን ማስተባቢያ ጠቅሶ ከታመኑ የዲፕሎማቲክ ምንጮቹ አገኘሁት ባለው መረጃ ቀደም ሲል የዝግጅት ክፍላችን በተደጋጋሚ እንደዘገበው ግለሰቡ ለመትረፍ የሚያሰጋ ሁኔታ ውስጥ ይገኛል ብሎአል።

ዘቴለግራፍ የተባለው ሌላው ታዋቂ ጋዜጣም እንዲሁ መለስ ዜናዊ በደም ካንሰር ህክምና ታዋቂ በሆነው በልጂዬም በሚገኘው የሴንት ሉክ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ውስጥ በመታከም ላይ እንደሚገኝና ሆኖም ግን የመትረፍ እድሉ የመነመነ መሆኑን የዲፕሎማቲክ ምንጮችን ገልጾ ዘግቦአል።

የአለም አቀፉ ሚዲያዎች የግቦት 7 ድምጽ ከሳምንት በፊት በእርግጠኝነት

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለ እኩልነት የወያኔው አገዛዝ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ላይ እየወሰደ ያለውን እርምጃ በመቃወም መግለጫ አወጣ

የግንቦት 7 የፍትህ፣የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ የአፋር ህዝብ ፓርቲና የኢትዮጵያ የአንድነትና የፍትህ ንቅናቄ ጥምረት (ጥምረት) ሃምሌ 10 2012 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ እንዳለው ዘረኛውና አምባገነኑ የመለስ ዜናዊ መንግስት ዜጎቹን የማሰቃየትና የመግደል የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው ነው። አሁንም በሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ላይ የፈጸመው ግድያ በአዲስ አበባ መብታቸው እንዲከበር በሰላማዊ ሰልፍ የጠየቁ 200 ኢትዮጵያዊያንን በመግደል የፈጸመው ታሪክ አምሳያ ነው።

በኢትዮጵያ ባህል የማምለኪያ ቦታዎች ተስፋ ላጡ መጠለያዎችና ቅዱስ ስፍራዎች ናቸው። ይሁንና ይሄ ጨካኝ ስርዓት ይህንን የተከበረ ሃይማኖታዊ እሴት በመርገጥ የተከበረውን የሃይማኖት ስፍራ ወደ ጦር ቀጠና ቀይሮታል ሲል ጥምረት በመግለጫው አብራርቷል።

ጥምረት ይህንን አረመኔያዊ የመንግስት ሽብርተኝነት ርምጃ በጽኑ ያወግዛል ያለው መግለጫው በዚህ በሰብዓዊ ፍጥረት ላይ በተፈጸመ ወንጀል ሰበብ ለሚከሰቱ ማናቸውም ጉዳቶችና ቀውሶች ብቸኛው ተጠያቂ የመለስ ዜናዊ መንግስት ነው በማለት አክሏል።

ባለፉት ስድስት ወራት የወያኔ ስርዓት ሃይማኖታዊ መሰረት ያላቸውን ተቋማት የቀን ተቀን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ያልተሳካ ሙከራ እንዳደረገ መግለጫው ጠቁሞ አሁንም ከሙስሊም ሃይማኖት ላይ እጁን እንዲያነሳ ጠይቋል።

ጥምረት የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ ህጋዊ ጥያቄዎቹን ፍጹም ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ መጠየቅና መፍትሄ ማፈላለግ በሀገሪቱ ውስጥ ለተፈጠረው አለመረጋጋት ብቸኛው አማራጭ ነው ብሎ ያምናል።በመሆኑም የወያኔ ስርዓት በልዩ ልዩ ማምለኪያ ቦታዎች ያሰፈራቸውን ወታደሮቹን እንዲያነሳ፣በዚህ ሳቢያ የታሰሩ ሙስሊሞችን በአስቸኳይ እንዲፈታና ወንጀል ፈጻሚዎቹንም ወደ ፍትህ አደባባይ የማቅረብ እንቅስቃሴ እንዲጀምር ይጠይቃል ብሏል።

በመጨረሻም መግለጫው ዓለም ዓቀፉ ለጋሽ ማህበረሰብ ይህንን በኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ኋላ ቀር ርምጃ እንዲያወግዝና የመለስን መንግስት በሰብዓዊ ፍጥረት ላይ ለፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ እንዲያደርገው፤ በሀገር ውስጥና በውጪ የሚገኙ መላ ኢትዮጵያዊያን ከሙስሊም ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጎን እንደቆሙ፤ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖችና የሌሎች እምነት ተከታዮችም ነጻነት፣ ፍትህና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ የሚሰፍነው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ ስርዓት ሲወገድ ብቻ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ይህንን አስከፊ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንዲታገሉ ጥሪ አስተላልፏል።

## የአምባገነኑ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ሙስሊሙን ህብረተሰብ ለመከፋፈል ከፍተኛ ሩጫ ላይ መሆኑ ታወቀ

በአወልያ የተጀመረው የሙስሊሙ እንቅስቃሴ እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ፣ የወያኔ የደህንነት ሃይሎች አንዳንዱን በግድ ሌላውን በመደለል በእየ ክፍለሀገሩ የሚገኙ ሙስሊሞችን ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ የድምጻችን ይሰማ መሪዎችን እንዲያወግዙ እያደረገ ነው በማለት ኢሳት በትናንትናው ዘገባው ዘግቦአል።

ኢሳት አንድ ስማቸው እንዳይገለጥ የፈለጉ የሙስሊም መሪ ለአዲስ አበባው ወኪሉ መንግስት በ1997 ዓም ቅንጅትን ከፋፍሎ ለመምታት የተጠቀመብትን ዘዴ በሙስሊሙ ላይ ተግባራዊ እያደረገ ነው ብለው መናገራቸውን ጠቅሶ ዘግቦአል። በየክፍለሀገሩ የሚገኙ ሙስሊሞች የአወልያውን እንቅስቃሴ እንዲያወግዙ እየተገደዱ መሆኑንም እኚሁ ሰው ተናግረዋል ብላአል ኢሳት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በመባል የሚጠራውና በህዝበ ሙሲልሙ ተቃውሚ እየቀረበበት ያለው አካል የተፈጠረውን ችግር ለማብረድ ሙከራ ያደርጋል ተብሎ ሲጠበቅ፣ ችግሩን የሚያባብስና ወደ ግጭት የሚያመራ ውሳኔ በትናንትናው እለት አሳልፎአል።

መጅሊሱ መጪው የጠቅላይ ምክር ቤት ምርጫ በቀበሌ መካሄድ ይገባዋል በማለት ከወያኔ አለቆቹ የተላለፈውን ውሳኔ እንደወረደ ተቀብሎ አጽድቋል።

ምክር ቤቱ በዋጣው የአቋም መግለጫ ላይ " ማህበረሰብ በአወናባጆች ሳይደናገር የምክር ቤቱን ውሳኔዎች እየተከተለ እንዲጓዝ ፤ የዋህብያና ሰለፊያ አክራሪ እምነት አራማጆች በአሁኑ ወቅት የሰደቃና የአንድነት ኮንፍረንስ እያሉ የሚያዘጋጇቸው ስብሰባዎች ከእምነቱ ጋር የሚጣረስ በመሆኑ ሃራም ነው" ሲል ገልጧል።

የወያኔ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒሰትር የሆኑው ሽፈራው ተክለማርያም "ባለፈው አርብ መዲናችን አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤን በምታካሂድበት ወቅት አክራሪ ሃይሎች ሆን ብለው ከተማዋን ለማተራመስ ያደረጉት ጥረት ዓላማቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ነው" በማለት የእምነት ነጻነታቸው እንዲከበር የጠየቁትን ዜጎች በጅምላ ወንጅሎአል።
ሽፈራው ተክለማሪያም "አንዳንድ አክራሪ ሃይሎች የእስልምና እምነትን ተገን በማድረግና የሰደቃ ድግስና የአንድነት ኮንፍረንስ በማዘጋጀት እኩለ ሌሊት ላይ ነዋሪዎችን ለሁከትና ትርምስ በመቀስቀስ በ19ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ስብሰባ ወቅት ከተማዋን ለማተራመስ አቅደው ነበር" በማለት የተለመደውን የወያኔ የፈጠራ ክስ አስምቶአል።

የሙስሊሙ ህብረተሰብ መብቱን ለማስከበር ቆርጦ መነሳቱ ያስደነገጠው ወያኔ በተለይ ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን አጋጭቶ የአገዛዝ እድሜውን ለማራዘም የተጓዘበት መንገድ መክሸፉ የመለስ ዜናዊ በመሃከላቸው አለመኖር ከፈጠረው ክፍተት ጋር ተዳምሮ ከፍተኛ ስጋትና ድንጋጤ ውስጥ እንደከተተው ብዙዎች ይስማማሉ።

## የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚንስቴር በልጂየም ውስጥ ከሞት ጋር ትንቅንቅ ይዞአል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የዘገበውን የመለስ ዜናዊን በህይወት መትረፍ አለመቻል ዜና በሰፊው እየዘገቡ ባሉበት በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ባለሥልጣናት እየሰጡት ያለው እርስ በርሱ የተምታታ መግለጫ በወያኔ መንደር የተፈጠረውን ድንጋጤና መረበሽ የሚያመለክት መሆኑን የዝግጅት ክፍላችን ካካሄደው ግምገማ ለማረዳት ተችሎአል።

ከበረከት ስምን፤ ሃይለማሪያም ደሳለኝና ሽማግሌው አቦስብሃት ለተለያዩ ሚዲያዎች ካለፈው ሰኞ ጀምሮ ሙሉ ያልሆነ መረጃ በመስጠት የአለቃቸውን መታመም አምነው ህመሙ ግን ለሞት የሚያበቃ እንዳልሆነ በየፊናቸው ተናግረዋል። ሽመልስ ከማል ከሳምንት በፊት በሰጠው ቃለመጠይቅ ጠቅላይ ሚንስትሩ ታሞአል በማለት የሚያስወራው ኢሳት ነው ሲል በዶር ካሱ ኢላላ የሚመራው የቤልጂዬም የወያኔ ኤምባሲ ደግሞ በበኩሉ ጠቅላይ ሚንስትሩ አልታመሙም፤ ወደ ቤልጂዬምም አልመጡም የሚል ጭፍን ምላሽ ጥያቀውን በኢሜል ላቀረበለት የዶቼቬሌ ሬድዮ መስጠቱን በትናንትናው ዕለት ሬዲዮው ዘግቦአል።

የመለስ ዜናዊን ኮማ ውስጥ ገብቶ ብራስልስ ከተማ በሚገኘው ሴት ሉክ ሆስፒታል ህክምና ላይ መገኘት ለዝግጅት ክፍላችን መረጃ ያቀበሉ ወገኖች እንደሚሉት ዶር ካሱ ኢላላም ሆኑ ሌሎች የቤልጂዬም ወያኔ ኤምባሲ ሰራተኞች መለስ ዜናዊ የተኛበት ሆስፒታል ሂደው እንዳይጎበኙ አብረውት በሚገኙ የደህንነት አባላት ስለተከለከሉ ትክክለኛ መረጃ ከማጣት በመነጨ ስሜት ሊሆን ይችላል ለዶቼ ቬሌ እንዲህ አይነት የተሳሳተ መግለጫ የሰጡት ሲሉ ወያኔ በቅጥረኝነት ለሚጠቀምባቸው ለእንደነ ካሱ ኢላላ ምንም አይነት ምስጥር እንደማያካፍል ለሚረዳው ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን ይህ ቅጥፈት የተሞላበት መልስ ወያኔ ላለፉት 21 አመታት በራሱና ለሆዳቸው ሲሉ በጥቅም በተጠጉት መካከል ከፈጠረው የጌታና ሎሌ ግንኙነት አኳያ ያልተጠበቀ እንዳልሆነ ግልጽ ነው ተብሎአል።

ሪፖርተር የተባለው አፍቃሬ ወያኔ ጋዜጣ በትናንትና እትሙ መለስ ዜናዊ ከአገር ውጪ በህክምና ላይ እንደሚገኝ ገልጾ፤ የህወሃት አባላት ካልሆኑት ባለስልጣኖች መካከል ግርማ ብሩና አባዱላ ገመዳ ካለበት ሆስፒታል ድረስ ተጉዘው ጉብኝተውት እንደተመለሱ ዘግቦአል። ሪፖርተር በማያያዝም ለደህንነት ጉዳይ ሲባል መለስ የት አገር ተኝቶ በመታከም ላይ እንደሚገኝ ምንጮቹ እንዳልገለጹለት ሃቲቶአል። ሪፖርተርን የመሰለ የመረጃ እጥረት የሌለበት ጋዜጣ አለም ያወቀውንና ጸሃይ የሞቀውን ሃቅ ለመሸፋፈን ሲል ቤልጂዬም የሚገኝ መሆኑን ስምቶ እንደማያውቅ በሚመስል ሳይዘግብ ማለፉ ብዙዎችን አስገርሞአል።

ይህ በዚህ እንዳለ የመለስ ዜናዊ መታመም በአባላቱና ደጋፊዎቹ ዘንድ በፈጠረው ስጋት በውጪ አገር በየ ኤምባሲው ተመድበው የሚገኙ ካድሬዎቹ እግራቸውን ለማውጣት ወደ ዬት አገር ሂደው ጥገኝነት ቢጠይቁ ተቀባይነት ሊያገኙ እንደሚችሉ በስደት ላይ ከሚያውቁዋቸው የቅርብ ጓደኞቻቸውና ቤተሰቦቻቸው ጋር መነጋገር መጀመራቸውን የደረሰን መረጃ አረጋግጦአል።

በአገር ቤትም እንዲሁ አንዳንድ ባለሥልጣናት ቤተሰቦቻቸውን ከአገር በተለያዩ ሰበቦች ማውጣት በመጀመራቸው የኢትዮጵያ አየር መንገድና ከኢትዮጵያ ጋር የበረራ ግንኙነት ያላቸውን አየር መንገዶች በሙሉ መጣበባቸው ተዘግቦአል።

የግንቦት 7 ንቅናቄ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን ድህሬ መለስ ዜናዊ የሚፈጠረው የዲሞክራሲ ሥርዓት ስዴትን፤ ጦርነትንና ድህነትን የሚቀርፍ እንዲሆን የአገራችን ፖለቲካ ያገባናል የሚሉ ሃይሎችን በሙሉ ያካተተ የሽግግር ሥር ዓት እንዲመቻች አቅሙ የቻለውን ሁሉ ትግል እንደሚያካሂድ እየገለጸ መሆኑ ይታወቃል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።
ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org